የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ

የሥራዝርዝርመግለጫቅጽ
I. አጠቃላይመግለጫ
የመስሪያ ቤቱ ስም የሥራ መደቡ መጠሪያ የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
ነርስ ፕሮፌስናል III

ነርሲንግ

የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር /ቢሮ ብቻ የሚሞላ
የሥራው ደረጃ የሥራው ኮድ

የክፍሉ ሃላፊ ነርስ /ነርስ ሱፐርቫይዘር XIII

መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ
በየደረጃው ባሉ የጤና ተቋማት
II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ውጤቶችና ተግባራት
2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡ -
• የህሙማን መረጃና የህክምና መገልገያ ግብዓቶችን ለሥራ ዝግጁ በማድረግ ፤ የህሙማን ክብካቤ ሥራዎችን በማቀድና በመስራት፣
አፈጻጸሙን በመከታተልና ለችግሮች የመፍትሔ ሃሳብ በማቅረብ፣ የምክር አገልግሎት በመስጠት፤ የተሻሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር ደረጃውን የጠበቀና ርህራሄ፡ጥንቃቄና አክብሮት የተሞላበት የነርስ ክብካቤ አገልግሎት እንዲኖር በማድረግና መረጃዎችን በማዘመን አገልግሎት መስጠት ነው፡፡
2.2. የሥራ መደቡ ውጤቶችና ተግባራት
ውጤት 1፡ የህሙማን መረጃና የህክምና መገልገያ ግብዓቶችን ለሥራ ዝግጁ ማድረግ፡፡
• የህሙማን አጠቃላይ ሁኔታና የህክምና መገልገያ ዕቃዎችን ከተረኛው በጽሑፍና በቃል ይረከባል፣ ያስረክባል፤
• በሥራ ክፍሉ ውስጥ ለቀንና ለማታ የሥራ ፕሮግራም ለሕሙማን ክብካቤና ሕክምና የሚያስፈልጉትን መድሐኒቶች፤ መሣሪያዎችንና
ሌሎች ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ እንዲሟሉ ያደርጋል፤
• በሥራ ክፍሉ የሚገኙ ንብረቶች ዝርዝር ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ይመዘግባል፣ ደህንነታቸውንም ይከታተላል፤
• መረጃዎችን በኮምፒዉተር ይመዘግባል ሪፖርት ይቀባበላል የህመምተኛዉን ሚስጥር በጠበቀ መልኩ መረጃ ይለዋወጣል፡፡

ውጤት 2፡ የነርስ እንክብካቤና የምክር አገልግሎት መስጠት፡፡
• የተለያዩ ክፍሎች ላይ ይሰራል ለምሳሌ በጨቅላ ህጻናት፤በስኳር ክፍል፤በነርቭ ክፍል በተቀላጠፈ መልኩ ይሰራል፣
• ለየህሙማንን ክፍል ንፅህና ይጠብቃል፣አልጋ ያነጥፋል፣ የተባለሹ የህሙማን አልባሳትን ያስወግዳል፤
• በራሳቸዉ የግል ንፅህና መጠበቅ ለማይችሉ የተኙ ህሙማን በመኝታቸው ላይ እንዳሉ ሰውነታቸውን ያጥባል፣ ባክ ኬር፣ ይሰጣል፣
• በራሳቸው መመገብ የማይችሉ ህሙማንን የተለያዩ የህክምና ዘዴዎች በመጠቀም በአፍንጫ፤በጨጎራ ቱቦ ይመግባል፣
• የቁስል ክብካቤ ይሰጣል (ይስፋል፤ክሮችን ያወጣል)፣
• የተለያዩ በነርስ የሚሰሩ ሁሉንም ፕሮሲጀሮችን ራሱን ችሎ ይሰራል ለምሳሌ በተቀላጠፈ ሁኔታ ያዋልዳል፤ጨቅላ ህጻናትን ክብካቤ ላይ
አድቫንስድ ፕሮሲጀሮች ራሱን ችሎ ይሰራል፣
• በተቀመጠው መመሪያና በሐኪም ትዕዛዝ መድኃኒቶችንና የህክምና ዓይነቶችን ለህሙማን ይሰጣል፣ የጎንዩሽ ጉዳታቸዉን ይከታተላል
የታማሚውን ሁኔታ በመከታተል ለሐኪሙ ገንቢ አስተያየቶችን ያቀርባል፤
• ለህሙማን ክብካቤ ያደርጋል፣ የህሙማንን የጤና ሁኔታ በመከታል መፍትሔ ይሰጣል፤
• በድንገተኛ አደጋ ወቅት ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በመሆን የህይወት አድን ተግባራትን ያከናውናል፤
• በተመላላሽና ተኝቶ ህክምና የሚታከሙ ሕሙማንን ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመለየት የሚፈቱበትን ሁኔታ ከሚመለከተው
አካል ጋር በመመካከር ያመቻቻል፤
• ቤተሰቦቻቸው ለሕሙማን ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያደርጉ ያበረታታል፣ ይመክራል፣ ያጽናናል፣
• ህሙማን በህክምና ላይ እያሉ ህይወታቸው ቢያልፍ አሰፈላጊውን የአስክሬን ክብካቤ ያድረጋል፤ አስክሬኑንም ያስረክባል፤ የህሙማንን መረጃ